**GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA**
**Office of the Chief Financial Officer**
**Office of Tax and Revenue**

ቀን፡ አክቶበር 1 2009

ለ፡ ሁሉም የዲሲ የሲጋራ ጅምላ ሻጮች

ጉዳይ፡ የሲጋራ፣ ሊትል ሲጋርና ሞይስት ስናፍ የኤክሳይስ ታክስ ጭማሪ

ቡሌቲን #፡ 2009 - 07

ከአክቶበር 1 2009 ጀምሮ የዲስሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሲጋራን ኤክሳይስ ቀረጥ መጠን ከፍ ያደርገዋል እንዲሁም ደግሞ በ "ሊትል ሲጋርስ" እና "ሞይስት ስናፍ" ላይ አዲስ ቀረጥ ይበይናል። የሲጋራን ኤክሳይስ ቀረጥ መጠን ለእያንዳንዱ ስጃራ ከ10¢ ወደ 12.5¢ ከፍ ያደርገዋል። ይህም አንድ 20 ሲጋራዎችን የያዘ ፓኮ ወደ $2.50 እንዲሁም አንድ 25 ሲጋራዎችን የያዘ ፓኮ ወደ $3.125 ከፍ ይላል። በ "ሊትል ሲጋር" ሽያጭ ወይም በለቤትነት ላይ ለእያንዳንዱ ሲጋር 12.5¢ ቀረጥ መከፈል ይኖርበታል። "ሊትል ሲጋር" ማለት፣ ፕሪምየም ሲጋር ያልሆነ፣ አንድ ሺ የሚሆን ከ 4 ½ ፓውንድ በላይ ክብደት ያለው ያሆነ ሲጋርን ያጠቃልላል። ሊትል ሲጋርን ለመሸጥ ወይም ባለቤት ለመሆን፣ ለእያንዳንዱ ሊትል ሲጋር 12.5¢ መከፈል ይኖርበታል። "ሞዩስት ስናፍ" ማለት፣ እንዲጨስና አፍንጫ ውስጥ ለመስገባት ተብሎ ያልተዘጋጀ፣ ያሆነ ደቆ የተከተፈ፣ የተፈጨ፣ ወይም ወደ ፓውደር የተቀየረ ትምባሆን ያመለክታል። የሞይስት ስናፍን ለመግዛት ወይም በንብረትነት ለመያዝ፣ ለእያንዳንዱ አውንስ 30¢ መክፈልና፣ ከአንድ አውንስ በታች ለሆኑ ደግሞ እንደየሚዛናቸው መጠን በተመሳሳይ ደረጃ ቀረጥ መክፈል ይኖርብዎታል።

አዲሱ የኤክሳይስ ቀረጥ ክፍያ የሚመለከተው፣ በቬንዲንግ ማሺኖች ውስጥ ያሉ ስጃራዎችን፣ እንዲሁም በዲሲ ውስጥ ለንግዳዊ የማከፋፈል ተግባር ተብለው፣ በጅምላ ነጋዴዎች፣ ቸርቻሪዎችና የጎዳና ቬንደሮች የተያዙ ወለል ላይ ያሉ የሊትል ሲጋሮችና የሞይስት ስናፍ ክምችቶችን ጨምሮ፣ የፍሎር ስቶኮች ይመለከታል። ቢሆንም፣ ሳብ ሆልሴይለሮችን (ምክትል-ጅምላ ሻጮችን) ሳይጨምር፣ በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉ የጅምላ ሻጮች፣ ከዲስትሪክቱ ውጭ ባሉ መጋዘኖቻቸው ውስጥ ላሉ የ "ሊትል ሲጋሮች" እና "ሞይስት ስናፍ" የፍሎር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ የለባቸውም።

በአክቶበር 1 2009 የንግድ ስራ ከመጀመርዎ አስቀድመው በስቶክ ውስጥ ያልዎትን የ ዲሲ ማህተም ያለባቸውን ሲጋራዎች የንብረት ቆጠራ(ፊዚካል ኢንቬንተሪ) ማድረግ ያስፈልግዎታል። ይህም የፍሎር ታክስዎን ለመወሰን ነው። ተመላሹንና ክፍያውን እስከ አክቶበር 1 2009 ድረስ ወደ Office of Tax and Revenue, Audit Division, Cigarette Tax Enforcement Unit, P.O. Box 556, Washington, DC 20044 ይላኩት። የወለል ቀረጥን (ፍሎር ታክስ) ሪተርን ፋይል ካላደረጉና እስከ አክቶበር 21 2009 ድረስ ካልተከፈለ በወንጀለኛነት ሊያስከስስዎት ይችላል። በተጨማሪ የያዙት የሲጋራ ላይሰንስ(ፍቃድ) ሊታገድብዎት ወይም ሊሰርዝብዎት ይችላል።

የኦፊስ ኦፍ ታክስ ኤንድ ረቨኑ፣ የኦዲት ክፍል የዲሲን ላይሰንስድ (ፍቃድ ያላቸውን) ጅምላ ሻጮች በኦክቶበር 21 2008 ወይም ከዚያ በፊት በፊዚካል ኢንቬንተሪ (ቆጠራ) ኦፍ ሲጋሬትስ በሚያካሂዱበት ጊዜ ይታዘባል። እባክዎትን ወደ ኦዲት ዲቪዠን በ(202) 442-6602 በመደወል ቀጠሮ ይያዙ።

የአዲሱ ስሌት የሲጋራ ታክስ ስታምፖስ ሮሎች ወይም ሽቶች ከየዲስሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ፣ ኦፊስ ኦፍ ፋይናንስ ኤንድ ትሬዠሪ ከሴፕቴምበር 25 2009 ጀምሮ መግዛት ይቻላል። እነዚህ ፓኮች ከኦክቶበር 1 2009 በፊት ስታምፕ የተደረጉ ቢሆኑም፣ ከዚህ ቀን በፊት መሸጥ የለባቸውም። የዲሲ የሲጋራ ቀረጥ ህግ እነዚህን ህጎች በሚጥሱ ላይ እርምጃ ይወስዳል። የተበላሹና “አሮጌ ማህተም” ያለባቸውን መሸጥ የሌለባቸው ሲጋራዎች ወደ ሲጋራ አምራቹ ከ ሴፕቴምበር 30 2009 አስቀድሞ መመለስ ያስፈልጋል። ይህም ከዲሲ ትሬዠሪ ክሬዲት ለመቀበል ያስችላል።

በዚህ ማስታወቂያ ወስጥ  ስለ ሲጋራ ፍሎር ታክስ  ተዘውትረው የሚጠይቁ ጥያቄዎች(ተ.የ.ጥ.) ሽት አቅርበናል። የዚህ ማስታወቂያ ቅጂና ተ.የ.ጥ.(የተለያዩ ትርጓሜዎች) በዌብሳይታችን ላይ በ www.taxpayerservicecenter.com ይገኛል።በተጨማሪም ዌብሳይታችን ስለ ፍሎርታክስ ሪተርንና መምሪያዎች አሉት።

ስለዚህ ህግ መቀየር በተመለከተ ጥያቄዎች ካልዎት ወደ ኦፊስ ኦፍ ታክስ ኤንድ ረቨኑ ኦዲት ዲቪዠን በ (202) 442-6602 ይደውሉ ወይም ደግሞ ወደ sherri.weithers@dc.gov ኢሜይል ይላኩ።

ለትብብርዎ እናመሰግናለን።